የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፵፭
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 45
ADDIS ABABA, 19th July , 2024

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፳፫/፪ሺ፲፮

በይነ-መንግሥታዊ የልማት ባለሥልጣንን ማቋቋሚያ ስምምነትን ማጸደቂያ አዋጅ...................................... ገጽ ፲፭ሺ፯፻፲፭

## Content

Proclamation **No**. 1323/2024

Inter-Governmental Authority on Development Establishment Agreement Ratification Proclamation…..…. …….…………….Page 15715

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፳፫/፪ሺ፲፮

### <u>በይነ መንግሥታዊ የልማት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ ስምምነትን ለማጸደቅ የወጣ አዋጅ</u>

መጋቢት ፲፪ ቀን ፩ሺ፱፻፹፰ የወጣው በይነ መንግሥታዊ የልማት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ ስምምነትን በማስፋት ዘላቂ ልማትን ለማስፈን ትብብርን ማጠናከር እና ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የተሻሻለው የኢጋድ መመሥረቻ ሰነድ ሰኔ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፭ ጅቡቲ በተካሄደው የመሪዎች ጉባኤ ወቅት የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህኑን ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ ፲ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአካሄደው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO. 1323/2024

### <u>PROCLAMATION TO RATIFY INTER-GOVERNMENTAL AUTHORITY ON DEVELOPMENT ESTABLISHMENT AGREEMENT</u>

**WHEREAS**, to replace the Agreement Establishing the Inter-Governmental Authority on Development dated 21st March 1996 to widen and deepen cooperation to achieve sustainable development;

**WHEREAS**, the Revised Agreement Establishing the Inter-Governmental Authority on Development (IGAD) was signed in Djibouti on the 19th Day of June 2023;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Agreement at its session held on 18th Day of April, 2024;

**NOW, THERERORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ “በይነ-መንግሥታዊ የልማት ባለሥልጣንን ማቋቋሚያ ስምምነትን ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፳፫/፪ሺ፲፮” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>**

ሰኔ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፭ ጅቡቲ የተፈረመው በይነ-መንግሥታዊ የልማት ባለሥልጣንን ማቋቋሚያ ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>አስፈጻሚ አካል</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በይነ-መንግሥታዊ የልማት ባለሥልጣንን ማቋቋሚያ ስምምነት የማስፈጸም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as “Inter Governmental Authority on Development Establishment Agreement Ratification Proclamation No. 1323/2024”.

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Agreement, signed in Djibouti on the 19th Day of June 2023 to establish the Inter-Governmental Authority on Development, is hereby ratified.

**3. <u>Implementing Organ</u>**

The Ministry of Foreign Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby empowered to implement the Inter-Governmental Authority on Development Establishment Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**DONE AT ADDIS ABABA, ON THIS DAY OF JUNE 19TH, 2023.**

**SAHALE - WORK ZEWEDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**